PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት
ኤጀንሲ

THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN INVESTMENT
AGENCY

2 ሚያዝያ 2007
ቀን
DATE

ቁጥር [illegible]/1/01
REF.No.

ለትግራይ ክልል ኢንቨስትመንት የሥራ ሂደት

ለአፋር ክልል ንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርትና የኢንቨስትመንት ቢሮ

ለአማራ ብ/ ክ/መ/ ንግድና ኢንዱስትሪ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ቢሮ

ለኦሮሚያ ክልል የኢንቨስትመንት ኮሚሽን

ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ

ለጋምቤላ ክልል ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ

ለሐረሪ ክልል ኢንቨስትመንት ማዕድንና ኢነርጂ ጽ/ቤት

ለቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልል ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት

ለሶማሌ ክልል ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ

ለአዲስ አበባ የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ

ለድሬዳዋ አስተዳደር ልማታዊ ባለሀብትን የመሣብና የማብቃት አብይ የሥራ ሂደት

ጉዳዩ፡- <u>የደንብ ቁጥር 270/2005 ማሻሻያ ደንብን እና አፈፃጸሙን ስለማሳወቅ</u>

ለባለሃብቶች የተሻለ ማበረታቻ ለመፍቀድ እንዲቻል ደንብ ቁጥር 270/2005 ደንብ ቁጥር 312/2006 በሚል ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም አንደገና ተሻሽሎ ወጥቷል፡፡

በክልል ደረጃ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ላወጡና በማምረቻ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች የጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ማበረታቻን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 10 መሠረት በክልል የኢንቨስትመንት መ/ቤት በኩል ማስተናገድ እንዲቻል ይህንኑ የሚያስፈጽሙ ከሁለት ያላነሰ ኃላፊ/ባለሙያ ከተመደበ በኋላ

ስልክ 011- 551 00 33
Tel. 011-553 72 86
✉ 2313
Website = www. ethioinvest.org
E-mail address = ethiopian.invest@ethioinvest.org
ፋክስ
Fax: 011-551 43 96

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

የፊርማ ናሙናቸው ተዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በማሳወቅ በአዋጁ አንቀጽ 30 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በማምረቻ ኢንዱስትሪ የሥራ መስክ ለተሰማሩ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በደንብ ቁጥር 270/2005፣ በደንብ ቁጥር 312/2006 እና በቦርድ መመሪያዎች መሠረት የክልሉ የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት የቀረጥ ነፃ መብት ውሳኔ እንዲሰጥ እናሳስባለን፡፡

በሌላ በኩል በግብርና እና በአገልግሎት የኢንቨስትመንት የሥራ ዘርፍ ላይ ለተሠማሩ የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች በመንግሥት በተለየ መልኩ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በደንብ ቁጥር 270/2005፣ በደንብ ቁጥር 312/2006 እና በቦርድ መመሪያዎች መሠረት የፕሮጀክቱ (የድርጅቱ) አፈጻጸም መግለጫ እና የድጋፍ ደብዳቤ በየክልሉ የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ለኢትዮጵያ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለሥልጣን በመላክ የቀረጥ ነፃ መብት ውሳኔው በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የሚሰጥ መሆኑን እየገለጽን፤ ለአፈፃፀም ይረዳ ዘንድ ሰኔ 7 ቀን 2006 ዓ/ም በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣውን ደንብ ቁጥር 312/2006 ፎቶ ኮፒ በዚህ ደብደቤ ሸኚነት አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

አባሪ፡- ደንብ ቁጥር 312/2006 (1 ኮፒ)

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ

- ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ
- ለኢትዮጵያ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለሥልጣን
  <u>አዲስ አበባ</u>

- ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮች
- ለጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ዳይሬክቶሬት

<u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን</u>

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ ነሐሴ ፯ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 62
ADDIS ABABA 13th August, 2014

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፲፪/፳፻፮ ዓ.ም

ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ........................ገጽ ፯ሺ፬፻፹፫

## CONTENTS

Regulation No. 312/2014

Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers (Amendment) Regulation.................................................Page 7483

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፲፪/፳፻፮**

**ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣውን ደንብ ቁጥር ፪፻፸/፳፻፬ ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፳፻፪ አንቀጽ ፭ እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፳፻፬ አንቀጽ ፴፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፫፻፲፪/፳፻፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 312/2014**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND THE INVESTMENT INCENTIVES AND INVESTMENT AREAS RESERVED FOR DOMESTIC INVESTORS REGULATION No.270/2012**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 39 of the Investment Proclamation No. 769/2012.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers (Amendment) Regulation No. 312/2014".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.35

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features



፪. ማሻሻያ

የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸/፪ሺ፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩/ በደንቡ አንቀጽ ፪ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፱) ተጨምሯል፤

"፱/ 'ነባር ድርጅት' ማለት የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም ሌላ አግባብነት ያለው ፈቃድ ኖሮት በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ ድርጅት ነው።"

፪/ ከደንቡ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ ውስጥ ከተራ ቁጥር ፩.፳ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር ፩.፳፩ ተጨምሯል፤

"

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ፩.፳፩ የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና (አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ከመንግስት ጋር ስምምነት በመድረስ የተቋቋመን የግል ኢንዱስትሪ ቀጠናን ጨምሮ) | ለ፲ ዓመት ከገቢ ግብር ነጻ የመሆን | ለ፲፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነጻ የመሆን |

"

፫/ የደንቡ አንቀጽ ፯ ነባሩ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፪) እና (፫) ተጨምረዋል፤

"፪/ በኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ባለሀብት ካቋቋመው የማምረቻ ፋብሪካ ፹ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን ምርት ወደ ውጭ የሚልክ ከሆነ ወይም ምርቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሃብት በምርት በግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ

2. **Amendment**

The Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulations No. 270/2012 is hereby amended as follows:

1/ The following new sub-article (9) is added under Article 2 of the Regulation:

"9/ 'existing enterprise' means an enterprise engaged in production or rendering services having a business license or any other appropriate license."

2/ The following new Item No. 1.21 is added after Item No. 1.20 of the Schedule attached to the Regulation:

"

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1.21 | Industrial development zone (including private industrial development zone investment, the establishment of which is agreed with the government prior to the issuance of the Proclamation) | Exemption from income tax for 10 years | Exemption from income tax for 15 years |

"

3/ The existing provision of Article 7 of the Regulation is renumbered as sub-article (1) and the following new sub-articles (2) and (3) are added:

"2/ An investor who has invested within an industrial development zone shall be entitled, in addition to what is provided for in sub-article (1) of this Article and the Schedule attached hereto, to 2 years income tax exemption if the investment is made in an industrial zone located in Addis Ababa or Special Zone of Oromia

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features



አንቀጽ (፩) እና ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ከሚያገኘው ማበረታቻ በተጨማሪ ኢንቨስትመንቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ወይም በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን በሚገኝ የኢንዱስትሪ ቀጠና ውስጥ ከሆነ ለ፪ ዓመት ወይም በሌላ አካባቢ በሚገኝ የኢንዱስትሪ ቀጠና ውስጥ ከሆነ ለ፬ ዓመት የገቢ ግብር ማበረታቻ ያገኛል፡፡

፫/ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ከመንግስት ጋር ስምምነት በመድረስ የተቋቋመ ወይም የሚቋቋም የግል ኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና ውስጥ የተሠማራ ወይም የሚሠማራ ባለሀብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ካሟላ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ የተመለከተውን ማበረታቻ ያገኛል፡፡"

፬/ የደንቡ አንቀጽ ፰ ተሠርዞ ከአንቀጽ ፱ እስከ ፲፰ ያሉት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፰ እስከ ፲፯ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

፭/ በደንቡ አንቀጽ ፲፪ (ቁጥሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት እንደተሸጋሸገው) ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፡-

"፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) በማምረቻ ኢንዱስትሪ ወይም በግብርና የሥራ መስክ የተሠማራና ቢያንስ ፪፻ ሺህ የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ ምንዛሪ ተመጣጣኝ የኢትዮጵያ ብር ካፒታል ኢንቨስት ያደረገና ቢያንስ ለ፶

surrounding Addis Ababa or to 4 years income tax exemption if the investment is made in an industrial zone located in other areas, provided that he exports 80% or above of the product from his manufacturing industry or supplies as production input to an investor who exports his products.

3/ An investor who has invested or is to invest within private industrial development zone, the establishment of which is agreed with the Government prior to the issuance of the Proclamation, shall be entitled to the incentive provided for in sub-article (2) of this Article upon fulfilling the preconditions stipulated therein."

4/ Article 8 of the Regulation is deleted and Articles 9 to 18 are renumbered as Articles 8 to 17, respectively.

5/ The following new sub-article (5) is added under Article 12 of the Regulation (as renumbered pursuant to sub-article (3) of this Article):

"5/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, any investor engaged in:

a) manufacturing industry or agriculture who has invested at least 200,000 United States Dollars or equivalent Ethiopian Birr at the prevailing rate of exchange and has created permanent employment opportunity

ኢትዮጵያውያን ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ ማንኛውም ባለሀብት ለነባር ድርጅቱ የሚያስፈልጉትን የካፒታል ዕቃዎች በማናቸውም ጊዜ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፤

ለ) በሌላ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ በሚፈቀድበት የሥራ መስክ የተሠማራና ቢያንስ ፪፻ ሺህ የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ ምንዛሪ ተመጣጣኝ የኢትዮጵያ ብር ካፒታል ኢንቨስት ያደረገና ቢያንስ ለ፶ ኢትዮጵያውያን ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ ማንኛውም ባለሀብት የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም ሌላ አግባብነት ያለው ፈቃድ ካወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ፭ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ለነባር ድርጅቱ የሚያስፈልጉትን የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል::"

፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ነሐሴ ፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

for at least 50 Ethiopian nationals shall be entitled to import, at any time, duty-free capital goods necessary for his existing enterprise;

b) another area of investment eligible for customs duty exemption and has invested at least 200,000 United States Dollars or equivalent Ethiopian Birr at the prevailing rate of exchange and has created permanent employment opportunity for at least 50 permanent employees shall be allowed to import duty-free capital goods necessary for the existing enterprise up to 5 years from the date of acquiring a business license or other appropriate license."

3. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 13th day of August, 2014.

HAILEMARIAM DESSALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features